# የሠላም ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ግንቦት/ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ፡መግቢያ ..... 2

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study) ..... 2

1.2. የዘርፉ አጠቃላይ ገፅታ ..... 3

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study) ..... 3

1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ፡- ..... 3

1.3.2. ንዑስ አላማዎች፡- ..... 4

1.4. የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ምንነትና ጠቀሜታው ..... 4

ክፍል ሁለት፡ የሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት የተዛማጅ ጹሁፎች ዳሰሳ ..... 5

2.1. በዘርፉ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ ..... 5

2.2. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች ..... 7

ክፍል ሦስት፡ የዘርፉ የጥናት ሰነ ዘዴ ..... 8

3.1. የጥናቱ ቦታ እና ወሰን ..... 8

3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰብያ ዘዴዎች ..... 8

3.3. ጥናቱ የተከናወነበት ሂደት ..... 9

3.4. የሙስና ስጋት ጥናት ስነ-ዘዴ ..... 9

3.5. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ ..... 10

3.6. የጥናቱ ተግዳሮቶች ..... 10

ክፍል አራት፡ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና ..... 10

4.1. የተቋማት አደረጃጀት ..... 10

4.2. ተጠያቂነት ..... 11

4.3. የተቋማት ግልጽነት ትንተና ..... 12

4.4. አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ ..... 12

4.5. የንብረት አስተዳደር ..... 12

4.6. የግዥ አስተዳደር ..... 13

4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር ..... 13

4.8. ሀብት ምዝገባ ..... 14

4.9. ፕሮጀክት አስተዳደር ..... 14

4.10. ኦዲትና ቁጥጥር ..... 14

4.11. የሙስና ስጋት ..... 14

ክፍል አምስት ፡ ምክረ ሀሳቦች ..... 15

ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች ..... 15

ማጣቀሻ ..... 18

አባሪ ሀ፡ የሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና ..... 19

# ክፍል አንድ፡መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጎዱ ችግሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ሙስና ማለት ባለስልጣኖች/ሀላፊዎች ከህብረተሰቡ የተሰጣቸውን አደራ ለግል መበልጸጊያ የማዋል ብልሹ አሰራር ማለት ነው፡፡ ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገወጥ ባህሪ ማለት ነው፡፡ ሙስና የህግ የበላይነትን በማጣመም እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ልማትን ያዳክማል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል፡፡ የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆል እና ህገ-መንግስታዊ ተቋማትን እና ስልጣንን አለማክበር የሙስና መገለጫዎች ናቸዉ፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት በተያዘው በጀት አመት ዘርፍ ተኮር አሰራርን በመከተል በ19 ዘርፎች ስር የሚገኙ ተቋማት የስራ አፈፃፀምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን ስጋቶችን በመለየት እና የመፍትሄ ሀሳቦችን መስጠት የሚያስችል ጥናት እያካሄደ ነው ፡፡

በተቋማት ለሙስና ስጋት እንደመነሻ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ሁኔታዎች ማለትም የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራረብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በመሆኑም ይህ የጥናት ሪፖርት በሰላም ዘርፍ በሚገኙ ሁለት ተቋማት ማለትም ሰላም ሚኒስቴር እና የብሔራዊ ተሀድሶ ኮሚሽን ሙስና ስጋት ሁኔታዎች ለመለየት በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በ11 ርዕሰ ጉዳዮች መሰረት ለተለዩ የሙስና ስጋቶች የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማመላከት ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ከሚገኙ ሁለት ተቋማት የብሔራዊ ተሀድሶ ኮሚሽን በአዲስ መልክ የተቋቋመ እና ገና በመደራጀት ላይ ያለ በመሆኑ ጥናቱ ትኩረት ባደረገባቸው ነጥቦች ላይ መረጃ ባለመኖሩ ይህ ትንተና በሰላም ሚኒስቴር በተሰበሰበ መረጃ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው ፡፡

## 1.2. የዘርፉ አጠቃላይ ገፅታ

ሙስና በማህበረሰቡ የሰላምና የፍትህ እኩል ተጠቃሚነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ሙስና የሰላምና ደህንነት ስጋት ምክንያት ነው፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ ሰላምና ደህንነት ከሌለ ዘላቂ ልማትን ማምጣት አይቻልም፡፡ ሙስና ማህበራዊ ቅሬታዎችን ያባብሳል፣ የመንግስትን ህጋዊነት ጥያቄ ውስጥ ይከታል፣ የተረጋጋ እና ሰላማዊ የሆነ ማህበረሰብ እንዳይፈጠር በማድረግ ሀገርን ስጋት ላይ ሊጥል ይችላል፡፡ የሰላም ዘርፍ በውስጡ የሰላም ሚኒስቴር እና የብሄራዊ ተሀድሶ ኮሚሽን ተቋማት የያያዘ ሲሆን ሁለቱ ተቋማት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263 /2014 የተቋቋሙ ሲሆን ተቋማቱ በህግ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር፣ በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል የሠላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የግንዛቤና የንቅናቄ ስልቶችን በመንደፍ ስራ የመስራትና በፌዴራልና በክልሎች መካካል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሰረተ የመልካም ግንኙነት ማዕከል እንዲኖር እንዲያግዝ የተደራጀ ዘርፍ ሲሆን ይህን እውን እንዲሆን የህዝብ ሰላም መጠበቁን ለማረጋገጥ አግባብነት ካላቸው የፌደራልና የክልል መንግስታት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡ በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል ሠላም እንዲሁም የመተባበር ባህል እንዲዳብር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን ቀይሶ ይተገብራል፤ ከባህልና ከሀይማኖት ተቋማት ጋር በቅርበት በመስራት ሠላምን የማስፈን ስራ ይሰራል፤ ለሰላም መከበር ከተለያዩ ሀይማኖቶችና ዕምነቶች ተከታዮች እንዲሁም አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

### 1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሰላም ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት ዘርፍ ተኮር የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

### 1.3.2. ንዑስ አላማዎች፡-

የዚህ ጥናት ንዑስ አላማዎች በሰላም ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት፡-1) የአሠራር ስርዓትን/የስራ አፈፃፀምን መገምገም፣ 2) የሙስና ተጋላጭነትን ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣ 3) ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ ሃሳቦችን ማስቀመጥ ናቸው፡፡

## 1.4. የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ምንነትና ጠቀሜታው

የሙስና ትርጉም፡1) በኦክስፎርድ ዲክሽነሪ፡- አደራን አለመጠበቅ፣ እምነት ማጉደል፣ በጉቦ፣ በምልጃና በአድሎ፣ ሐቅን፣ ውሳኔን ወይም ፍትህን ማዛባት፡፡ 2) በካቶ (1996)፡- ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል፣ ሥርዓቶችን፣ ደንቦችን፣ ህጐችንና መርሆዎችን መጣስ ነው፡፡ 3)የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ 1993:- የመንግስትን ሥራ ሥነ ምግባራዊና ህጋዊ መሠረት ባለው መመሪያና ደንብ ላይ ተመርኩዞ አለመስራት፡፡ 4) Transparency International፡- በመንግስትና በህዝብ የተሰጠን ሥልጣንና ኃላፊነት ለግል ጥቅም፣ ወይም ሌላን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲባል በስልጣን አለአግባብ መገልገል ነው፡፡ ሙስና ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ከመስራት ይልቅ ስልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ ህግና ሥርዓትን በመጣስ የመንግስትና የህዝብ ሃብትና ንብረትን መስረቅ፣ መዝረፍ፣ ማጭበርበር እንዲሁም በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትውውቅ በጉስኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነትና በኃይማኖት ትሥሥር በመመርኮዝ ፍትህን እያዛቡ የግል ጥቅምን ማካበትና ሌላውን ወገን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጥቀም ወይም መጉዳት ነው፡ ፡

ግለሰቦች ወደ መንግስት ሃላፊነት በሚመጡበት ጊዜ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በህግና በአግባብ እንዲጠቀሙበት ቢጠበቅም ይህንን ሃላፊነት ለግል ጥቅም ማካበቻ የሚያውሉበት ሁኔታ ካለ ሙስና ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሙስና የግል ጥቅምን ለማግኘት በሚል ሃላፊነትን ባግባቡ አለመጠቀም ወይንም ሃላፊነትን ተጠቅሞ ያልተገባ ነገር ማድረግን ይመለከታል፡፡ ሃላፊነትን ለግል ጥቅም ማዋል በሚለው እይታ ውስጥ በርካታ ተግባራት ሊዘረዘሩ ይችላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 881/2015) 25 የሙስና ወንጀል ተግባራት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ የዚህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ጠቀሜታው፡-ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ተከስተዉ ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሳቸዉ በፊት ለችግሩ ክፍተት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መርምሮ በማዉጣት የመፍትሄ ሀሳቦችን በማቅረብ ችግሮች ከወዲሁ እንዲቀርፉ ለማድረግ ያስችላል፡፡ የዚህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ጠቀሜታው፡-ይህንን ጥናት ስፖንሰር ያደረገው የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እስከሆነ ድረስ ለሙስና የተጋለጡ ዘርፎችን በመለየት ቀጣይ ዝርዝር የሙስና መከላከል ጥናቶችን ለማካሄድ ኮሚሽኑ በራሱ መንገድ ለፖሊሲ ግብአት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለቀጣይ ከሙስና ጋር በተያያዘ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ አንድ ማጣቀሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

# ክፍል ሁለት፡ የሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት የተዛማጅ ጹሁፎች ዳሰሳ

ሙስና የማህበራዊ ቅሬታዎችን በማባባስ የመንግስትን ስርዓት ያበላሻል፣ የተረጋጋ እና ሰላማዊ ማህበረሰብ እንዳይፈጠር በማድረግ የህዝብ አገልግሎቶችን ሊያጓድል ይችላል፡፡ የጸረ-ሙስና አካሄዶች ሰፊ የሆነ የሲቪክ ማህበራት እና የዜጎች መብቶች ላይ ያነጣጠረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዲሁም መረጃ የማግኘት መብት እና የመንግስት ግልጽ አቀራረቦችን ያካትታሉ (BMZ እና ሌሎች 2019)፡፡ ሙስና የህዝብ ቅሬታዎችን እና የፖለቲካ ለውጥ ጥያቄዎችን ይጨምራል (Mauro, 1995)፡፡

## 2.1. በዘርፉ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

ሥርዓታዊ ሙስና ከአመጽ እና ከግጭት በሚወጡ አገሮች ውስጥ ሥር የሰደደ ችግር ነው (Cheng & Zaum, 2013; Lindberg & Orjuela, 2014)፡፡ ሙስና ከግጭት በኋላ ካለው የሰላም ጥረት ጋር ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ግንኙነት አለው (ግሎባል የሰላም መረጃ ጠቋሚ፣ 2015)፣ ሙስና የኀሳ ግጭት ስጋትን ይጨምራል (Neudorfer & Theuerkauf, 2014)፡፡ በአጠቃላይ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ልማት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል (ኤዲት፣ 2003)፡፡ የብዙዎቹ የድህረ-ግጭት ሀገራት ደካማ ተቋማትን በመፍጠር የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለግል ጥቅም ለማዋል ለሚፈቅዱ ተግባራት ለሙስና ተስማሚ የሙስና መፈጠሪያ ስፍራዎች ናቸው (ስቬንሰን፣ 2005) ፡፡

ሙስና፣ የፍትህ እጦት እና የተለያዩ ግጭቶችን በመፍጠር ወጣቶችን ወደ ህገወጥ ቡድኖች እንዲቀላቀሉ እድል ፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ ወጣቶች በሶማሊያ አልሸባብን፣ በአፍጋኒስታን ታሊባንን እቅፍ ውስጥ እንዲገቡ የሚገፋፉ ምክንያቶች እንደነበሩ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ሀገራቱ ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ ከሆነ ሙስና ጋር ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ በ2015 ሶማሊያ እና አፍጋኒስታን ከሰሜን ኮሪያ በመቀጠል የመጨረሻዎቹን ደረጃ ይዘዋል(Belloni 2014)፡፡ ሙስና በሰላም ግንባታ ላይ ለመስራት የሚደረጉ ሙከራዎችን አቅም ያዳክማል (GIZ, 2020)፡፡ በሀገራት የሙስና መስፋፋት ምክንያት ሙስናን የመከላከል፣ የመመርመር እና የወንጀል ተጠያቂነት ቀጥተኛ ተልእኮ የተሰጣቸው ተቋማት ውጤታማ ባለመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ የፀረ-ሙስና ተቋማቱ ሕገ መንግሥታዊ ከለላ እና ተቋማዊ ነፃነት ስለሌላቸው ነው፡፡ ሙስና ከብሔር ፖለቲካ ጋር ተያይዞ ለሰላም ትልቅ ስጋት ነው፣ ለሀገሪቱም ህልውና ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ አለው (ዘመላክ፣ 2017) ፡፡

ሙስና ግጭትንና አለመረጋጋትን ሊፈጥርና ሊያባብስ ይችላል፡፡ ሙስና የመንግስትን ውሳኔን በማዛባት የህዝብ አገልግሎቶችን የሚያበላሽ በመሆኑ ሙስና ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ቅሬታዎችን በተለይም የእኩልነት እና የፍትህ እጦት ስሜትን ሊያባብስ ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል፣ በአረብ ጸደይ አመጽ፣ ሙስና ሰፊ ቅሬታዎችን የፈጠረ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፣ ይህም በተለያዩ መንግስታት ላይ ህዝባዊ ንቅናቄን አመቻችቷል (ቺብዋና 2008)፡፡ ሙስና የመንግስትን አገልግሎት ከሚያቀርቡ ተቋማት ወደ ግል ጥቅም መጠቀሚያ የሚውል ተቋም

ሊፈጥር ይችላል (አሚናል 2006)፡፡ በሞሮኮ ውስጥ በሙስና ላይ የተደረገ ጥልቅ ጥናት እንዳመለከተው ሙስና የአገሪቱን ኢኮኖሚዊ፣ ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ ብቃቷን አዳክሟል (ክሊትጋርድ 1988)፡፡ በዚሁ መሰረት በጋና የተደረገ ሌላ ጥናት እንዳመላከተው ሙስና የጎሳ ግጭቶችን ያጠናክራል፣ የክልል እና የፌደራል ተቋማትን ግንኙነት በማበላሸት የመልካም አስተዳደር ችግር እንደፈጠረ አረጋግጧል፡፡

በአለም ላይ ሙስናን በመዋጋት ከፍተኛ ውጤት ያመጡ እና ለሌሎች ሀገራት አርአያ መሆን የቻሉ ሀገሮች መካከል፡- የሲንጋፖር ፀረ ሙስና ተቋም በ1952 የሙስና ተግባራት ምርመራ ቢሮ (CPIB) ሲሆን በፀረ ሙስና ትግሉ ውስጥ የተገኘው ስኬት በዋናነት በሶስት ምክንያቶች እንደነበር ይገለጻል፡፡ እነእሱም፡- ከመንግስት ጠንካራ የፖለቲካ ፍላጎት፣ በቂ የህግ ማዕቀፍ እና የተግባር ነፃነት (ኳህ፣ 2001) ናቸው፡፡ የሆንግ ኮንግ ፀረ-ሙስና ተቋም በ1974 የተመሰረተ ሲሆን ጥንታዊ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ በጣም ስኬታማ ተቋም ነው፡፡ ገለልተኛው የሙስና ኮሚሽን (ICAC) በርካታ የቅጣት ውሳኔዎችን ያስገኙ የምርመራ ሪከርድ ገንብቷል (ሄይልብሩን፣ 2004)፡፡ በትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የቅርብ ጊዜ የሙስና ግንዛቤ ኢንዴክስ መሰረት፣ ሆንግ ኮንግ በሙስና አነስተኛ ከሚባሉ የአለም ሀገራት ተርታ ትገኛለች፡፡ የሆንግ ኮንግ (ICAC) በግዛቱ እስካሁን የተንሰራፋውን ሙስና ለመግታት በተመሳሳዩ ምክንያቶች የተነሳ ውጤታማ ነበር (ማሪያ፣ 2002)፡፡ ከሆንግ ኮንግ እና ሲንጋፖር ቀጥሎ ኢንዶኔዢያ በፀረ ሙስና እንቅስቃሴዎች ውስጥ የስኬት ታሪክ ሆኖ ተጠቅሷል፡፡ በ2002 የተቋቋመው የኢንዶኔዥያ የሙስና ማጥፋት ኮሚሽን (KPK) በሙስና የተዘፈቁ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ላይ 100 % የሚጠጋ የቅጣት መጠን ላይ በመድረሱ ከፍተኛ አድናቆትን አግኝቷል (Transparency International, 2013)፡፡

በ1990ዎቹ አጋማሽ የተቋቋመው የላትቪያ የሙስና መከላከል እና መዋጋት ቢሮ (KNAB) አሁን እንደ አውሮፓ በጣም ቀልጣፋ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በከፍተኛ የፖለቲካ መሪዎች መካከል ያለውን ሙስና ለመመርመር ባሳየው ቁርጠኝነት ከፍተኛ አድናቆት ተችሮታል፡፡ ወደ አፍሪካ ስንመጣ የቦትስዋና የፀረ-ሙስና ተግባራት ታሪክ በጣም የሚያስመሰግን ነው፡፡ ሀገሪቱ ሙስና እና ሌሎች ተያያዥ ወንጀሎችን ለመከላከል በ1994 ዓ.ም የሙስና እና ኢኮኖሚክስ ወንጀሎች ዳይሬክቶሬትን መስርታለች፡፡ ቦትስዋና አሁን ከሰሃራ በስተደቡብ ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ትንሿ ሙሰኛ ሀገር ሆናለች (Mail & Guardian Africa, 2014)፡፡ ምንም እንኳን በኢንዶኔዢያ፣ በላትቪያ እና በቦትስዋና የፀረ-ሙስና ተቋማት የራሳቸው ልዩ ገፅታዎች ሊኖራቸው ቢችልም ለስኬታማነት ያበቃቸው እንደ ሆንግ ኮንግ እና የሲንጋፖር ፀረ ሙስና አካላት በጋራ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠራቸው ነው፡፡

## 2.2. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች

ለአለም ሰላም አለመረጋጋት በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ከነዚህም መካከል፡- (ሀ) የስራ አጥ ቁጥር መጨመር፣ የህዝብ ፍላጎቶች አለመሟላት፣ የፖለቲካ መብቶች መከልከል፣ አግላይ በሆነ መንገድ ሀብትን ወደ ሌላ ቦታ የሚቀይሩ የታጠቁ ቡድኖች ወደ መንግሥት እንዲገቡ ወይም ሀብታቸውን እንዲያሳድጉ መፍቀድ ነው፡፡ አብዛኞቹ ሙስና የተስፋፋባቸው አገሮች ከሚያጋጥማቸው ችግሮች መካከል ሙስናን የመመርመር ነፃነት ማጣት፣ ህብረተሰቡ ለሙስና ግድየለሽነት፣ በህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ውስጥ የተንሰራፋ ሙስና፣ ሙያዊ ብቃት እና ቁርጠኝነት ማነስ እና ሙስናን በመዋጋት ስትራቴጂካዊ አጋርነት አለመኖሩ ይገኙበታል (UNOCD, 2004)፡፡ የተለያዩ የማህበረሰብ ውይይቶችን ከፀረ ሙስና ጋር በማጣመር ግልፅነትና ተጠያቂነት ላይ በማተኮር ሰላምን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ሊደግፍ ይችላል፡፡ በማህበረሰቦች እና በተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት እንደገና በመመሥረት፣ በቡድኖች መካከል መተማመንን ለመገንባት፣ ግጭቶችን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት፣ በተቋማት ላይ እምነትን ለማደስ እና ማህበራዊ ተጠያቂነትን የማጎልበት አቅም አላቸው፡፡ የተሳለጠ ውይይት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ችግር ለመፍታት እና ከአስተዳደር መርሃ ግብሮች ጋር በማጣመር ለዜጎች ጥያቄዎች እና ተጠያቂነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ፍላጎት ምለሽ ሊሰጥ ይችላል (ሆፕ-ኒሽካ 2021b)፡፡

የፀረ-ሙስና ተቋማት ውጤታማነት መስፈርቶች መካከል ተቋማዊ ነፃነት አንዱ ሲሆን በቂ ሀብቶች፣ ሁሉን አቀፍ ትእዛዝ፣ ግልጽነት፣ በቂ የምርመራ ሃይሎች እና ትብብርን ያጠቃልላል፡፡ ሙስናን መዋጋት ያለብን ዘርፈ ብዙ በሆነ ስልት ነው ምክንያቱም ተፈጥሮው፣ መጠኑ እና ቅርፁ ከቦታ ቦታ ስለሚለያይ ይህንን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎች ስለሚለያዩ ነው (ሺመልስ፣ 2005)፡፡ በአለም ላይ ሁሉንም አገሮች የሚያስማማ አንድም ሞዴል ወይም አሠራር የለም (UNCAC፣ 2003)፡፡ ስለዚህ ሙስናን የመቆጣጠር ስትራቴጂ የችግሩን ስፋት፣ መንስኤዎቹንና ሙስና ሊፈጠር የሚችልባቸውን አካባቢዎች በግልፅ በመረዳት መጀመር አለበት (ሽመልስ፣ 2005)፡፡

ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እና ለመቀነስ ስልቶችን ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት የፀረ-ሙስና ትግሉን የሚያደናቅፉ ዋና ዋና ችግሮች ወይም እንቅፋቶች መለየት አለባቸው (Wing-chi, 2014)፡፡ እነዚህን ችግሮች ለይተው ካወቁ በኋላ፣ አጠቃላይ የፀረ-ሙስና ስትራቴጂክ ዕቅዱን አውጥተው ወደ ትግበራ መተርጎም አለባቸው፡፡ ለዚህ ዓላማ እንደ ዊንግ-ቺ (2014) ያሉ ምሁራን፣ አንድሪው (2013)፣ ICAC (2009) እና እንደ ቶኒ ክዎክ ማን-ዋይ የቀድሞ የICAC ምክትል ኮሚሽነር ያሉ ባለሙያዎች የተለያዩ ሀገራት የሆንግ ኮንግ ሞዴል ICACን ስልቶችን እንዲከተሉ ይመክራሉ፡፡

በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የሀገሪቱ የፖለቲካ ስርዓት መንግስታዊ በሆነ ኢኮኖሚ መያዝ፣ ለግል ጥቅም የሚያገለግል የፖለቲካ አመራር መኖር፣ አቅጣጫ የለሽ እና ውጤታማ ያልሆነ የመንግስት መዋቅር፣ ደካማ እና ለአደጋ የተጋለጡ ብሄራዊ የአስተዳደር ተቋማት፣ እንደ ፓርላማዎች፣ የፍትህ አካላት እና የሙስና ተቆጣጣሪ ተቋማት በኢትዮጵያ ለሙስና መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል (ከበደ፣ 2013) ። በዚህ ጥናት መሰረት ተግዳሮት ናቸው ተብለው ከተገለጹት ችግሮች መካከል፡- የነጻነት እጦት፣ የሰራተኞች ውስንነቶች፣ የህዝብ አሉታዊ አመለካከት፣ ደካማ የህግ ማዕቀፎች እና የዳኝነት ሂደቶች ዘገምተኛ መሆን፣ በቂ የገንዘብ፣ የሰው እና የቴክኒክ ሃብት፣ የግልጽነት ጉድለት፣ ሰፊና ግልጽ የሆነ ስልጣን አለመኖር፣ በቂ የምርመራ ስልጣን እና ትብብር ማነስ፣ በቂ ያልሆነ ቅስቀሳ እና የዜጎች ተሳትፎ ማነስ፣ ለሙስና በቂ የሆነ ትኩረት ሰጥቶ አለመስራት ናቸው።

# ክፍል ሦስት፡ የዘርፉ የጥናት ስነ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ቦታ እና ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በፌዴራል ደረጃ በሚገኙ ዘርፎች ያለው የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናት ለማካሄ ሲሆን በእያንዳንዱ ዘርፍ ስር በሚገኙ የመንግስት መሰሪያ ቤቶች ተቋማት ያከተተ ሲሆን ጥናቱ በአዲስ ከተማ በሚገኙ ተቋማት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ።

## 3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰብያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል። የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች በመጠይቅ እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው። ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል።

**መጠይቅ፡-** የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃሊፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈሊጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሉስት እንዲሞለ ተደርጓል። ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምሊሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው። በሌላ አገላለፅ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው።

**ሰነዶች፡-** የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል።

**የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት፡-** እንደሚታወቀው የሙስና ስጋቶች ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም የመለያየት ባሕሪ አላቸው፡፡ ስለሆነም ተቋም-ተኮር የሙስና ስጋት ልየታ ለማካሄድ በጥናቱ በተካተቱ ተቋማት ውስጥ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል ፡፡

## 3.3. ጥናቱ የተከናወነበት ሂደት

ይህን ጥናት ለማከናወን በአማካሪዎች፣ በጥናት ቡድን መሪዎችና በመረጃ ሰብሳቢዎች አማካኝነት ሶስት ዋና ዋና ሂደቶችን የተከተለ ሲሆን አንደኛው የጥናቱ መጠይቅ ዝግጅት ሲሆን መጠይቁን ለማዘጋጀት የተለያዩ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተሞክሮወችን እና ተያያዥ ጽሁፎችን በመዳሰስ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል፡- የተዘጋጀውን መጠይቅ የሚመለከታቸው አካላት እንዲወያዩበት እና እንዲፀድቅ ተደርጓል፣ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለጥናት ቡድን መሪዎች የስልጠና ሞጁል በማዘጋጀት ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በሁለተኛው ምዕራፍ የመረጃ መሰብሰብ ሂደት ሲሆን የመረጃው አሰባሰብ ሂደት በሁለት ዓይነት ዘዴ የተዘጋጀ ሲሆን 1ኛ) በሃርድ ኮፒ እና 2ኛ) በሶፍት ኮፒ የተቋማት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የመረጃዉን ተአማኒነት ለማረጋገጥ ሁሉም መጠይቆች መረጃ ከተሞላባቸዉ በኋላ ከተሰበሰበው የሰነድ ማስረጃ ጋር እንዲረጋገጥ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም መረጃው ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት የመረካከቢያ ፎርም በማዘጋጀት ያልተሟሉ መረጃዎች እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ተገቢ የሆኑ የስነ-ምግባር መርሆችን በመከተል፡- የግለሰቦችንም ሆነ የተቋምን መብት የማይጋፋ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንዲሁም የመረጃዉን ሚስጥራዊነት  እንዲጠበቅ ተደርጓል፡፡ የሶስተኛው ሂደት የሪፖርት ዝግጅት ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ስለ ሪፖርት አጻጻፍ ለጥናት ቡድን መሪዎች እና አባላት ስልጠና ተሰጥቷል፣ በስልጠናው መሰረት የተዘጋጀውን ረቂቅ ሪፖርት ቀርቦ የሚመለከታቸው አካላት እነዲወያዩበት እና እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

## 3.4. የሙስና ስጋት ጥናት ስነ-ዘዴ

የተለያዩ የዓይነታዊ የመረጃ ትንተና ስልቶች መካከል አንዱ የሆነውን ቲማቲክ (ጭብት ተኮር) የምርምር ዘዴ የተጠቀምን ሲሆን ይህ የጥናት ዘዴ በመረጃ ውስጥ ፓተርንን (ርዕስን) የመለየት፣ የመተንተን እና ሪፖርት የማድረግ ዘዴ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የመረጃውን መጠን የሚቀንስ ገላጭ የሆነ የትንተና ዘዴ ነው፡ ፡ ይህ አካሄድ የተለያዩ ዘዴዎችን ሊያካትት ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የዳሰሳ ጥናት መጠይቆች፣ የቡድን ውይይቶች እና በተለያዩ የጽሑፍ ስብስቦች ላይ ይተገበራል፡፡ ጭብጥ ትንተና ዘዴን በመጠቀም ተመራማሪው በጽሁፎቹ ውስጥ በተገለጹት ርእሶች እና ሃሳቦች ላይ ተደጋጋሚ ንድፎችን ወይም ጭብጦችን ለመለየት የመረጃ ስብስብ ያጠናል፡፡ የዓይነታዊ መረጃዎችን በመተንተን፣ የቲማቲክ (ጭብጥ ተኮር) ትንተና በፅንሰ-

ሀሳቦች፣ አስተያየቶች እና ልምዶች ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ውስብስብ፣ ገላጭ እና በተለያዩ ፍልስፍናዊ እና ፅንሰ-ሀሳባዊ መሠረቶች ላይ ሊጣበቅ የሚችል የመረጃ አቀራረብን የሚጠይቅ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሙስና ስጋት ደረጃን ለመተንተን የአሀዛዊ መረጃ የትንተና ዘዴ የሆነውን የሙስና ስጋት ማትሪክስ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## 3.5. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) እና (Corruption risk matrix) አሀዛዊ መረጃዎችን ለመተንተን ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (መጠይቅ፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎሌበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ዘዴን ተጠቅሟል፡፡

## 3.6. የጥናቱ ተግዳሮቶች

ጥናቱ የተለያዩ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል እነሱም፡-የተቋማት ኃላፊዎች/ ሰራተኞች በተያዘላቸው ቀጠሮ ያለመገኘትና ጥናቱን የሚያከናውኑትን ባለሞያዎች የማመላለስ፣ አዲስ ተቋማት ያሉ በመሆናቸው መረጃው በበቂ ሁኔታ በመወሰድ የዘርፉን ሁኔታ ለመገመገም እክል መፍጠሩ፣ የተሟላ ሰነድ ያለው መረጃ ያለማቅረብ፣ የተቋማት ኃላፊዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን እና የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በሌላቸው ተቋማት የተደራጀ መረጃ ለማግኘት አሰቸጋሪ መሆን ናቸው፡፡

# ክፍል አራት፡ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና

የሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት ትንተና በአስር ርዕሰ ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4.1. የተቋማት አደረጃጀት

በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት ሰላም ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና አስፈጻሚ ክፍል ያቋቋመ መሆኑን በምልከታ የተረጋገጠ ሲሆን ክፍሉን በሰው ኃይል ከማሟላት አንጻር 75% የተሟላ መሆኑን እና ለባለሙያዎችም በቂ ቢሮ እና ምቹ የስራ ቦታ የተፈጠረ መሆኑን በምልከታ ተረጋግጧል፡፡ በጀትን በሚመለከት ክፍሉ ራሱን የቻለ የተመደበ በጀት ባይኖረውም ከሌሎች ክፍሎች ጋር በጋራ (ፑል) አሰራር እንደሚጠቀም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የመከታተያ ክፍሉም የ2015 በጀት አመት የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል እቅድ ያዘጋጀ መሆኑን በቀረበው ሰነድ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተቋሙ የሀብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ በማደራጀት ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል አጋዥ አሰራር መኖሩ ከቀረበው ሰነድ ለማየት ተችሏል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ዘዴ ከመጠቀም አንጻር በዘርፉ ካሉት ተቋማት የሰላም ሚኒስቴር ስርአት መዘርጋቱን በምልከታ ለማየት የተቻለ ሲሆን የተደራጀው የመከታተያ ክፍል ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት አግባብ እንዳለ በተገኘው ሰነድ ተረጋግጧል፡፡ የሕግ ክፍል በሚዘጋጁ ውሎች ላይ ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት እንደሚሰጥ የሚያመለክት መረጃ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ካሉ ተቋማት በሰላም ሚኒስቴር በስነምግባር መከታተያ ክፍል አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ስለመኖሩን የሚያሳይ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ከተቋማዊ አደረጃጀት አኳያ የዘርፉ አዲስ ተቋማት የስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ላይ ፈጥኖ ያለመግባት፣ ተቋማት የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሉ ራሱን የቻለ የተመደበለት በጀት አለመኖሩ እና በበቂ የሰው ሃይል ባለመሟላቱ ስራውን በውክልና እንዲሰራ መደረጉ፣ ዘርፉ ለስነምግባር ግንባታ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ተግባር ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ እንዲሁም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሃብት ወይም ንብረት እንዲመዘበር፣ እንዲወሰድ፣ ወይም እንዲጠፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 4.2. ተጠያቂነት

ዘርፉ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን አሰራር ጥናት ከማካሄድ አንፃር በሠላም ሚኒስቴር የአሰራር ስርአት ጥናት መካሄዱን ከተገኘው መረጃ ለማየት የተቻለ ሲሆን ጥናቱን ተመርኩዞ የማሻሻል እና የማረም ስራም መከናወኑን ሰነዶች ያሳያሉ፡፡ የደንበኞች እርካታን በተመለከተ በገለልተኛ አካል ስለመጠናቱ እና የሥነምግባር መመሪያ (Code of conduct) ስለማዘጋጀታቸው የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት በሚደርሱ ጥቆማዎች መሰረት ቅድመ-መከላከል ስራ አለመኖሩ ተገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በሥነምግባር ጉድለት ሶስት አመራር እና ሁለት ባለሙያዎች የተከሰሱ ስለመሆኑ በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በህግ ክፍሉ አምስት ክሶች ቀርበው ሶስቱን ወይም 60 % ተቋሙ ያሸነፈ መሆኑን እና ውሳኔ የተሰጠበት ሰነድ መኖሩን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሌላው የቅሬታ አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ ሶስት ቅሬታዎች ቀርበው ሶስቱም የተፈቱ መሆኑን መረጃዎች ሲያሳዩ የበላይ ኃላፊዎች የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍልን የስራ ክንውን መገምገማቸውን አስመልክቶ ሌሎች ክፍሎች ጋር በጋር የሚገመገም መሆኑን እንጂ በተናጥል ክፍሉ የሚገመገም መሆኑን የሚሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡

የተቋማትን ተጠያቂነት ከማረጋገጥ አንፃር የስነ ምግባር መከታተያ ክፍል ለብቻው ትኩረት ተሰጥቶ አለመገምገሙ ክፍሉ ያሉበትን የአሰራር ክፍተቶች ለይቶ እንዲያውቅ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል አቅም እንዳይኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንዲሁም የደንበኞችን እርካታ በገለልተኛ አካል አስደገፎ ያለማስጠናቱ በተቋሙ ያለውን የደንበኞች አገልግሎት ሁኔታ፣ የአሰራር ክፍተቶችን እና ተቋሙ በደንበኞች አገልግሎት ዙሪያ የማሻሻያ ስራ እንዳይሰራ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## 4.3. የተቋማት ግልጽነት ትንተና

በዘርፉ ካሉት ተቋማት መካከል ሰላም ሚኒስቴር ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ማዘጋጀቱን እና ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት መደረጉን እና ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አፈጻፀም ላይ ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር እንደተገባ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው ብልሹ አሰራሮችን ከመለየት አንፃር ማናጅመንቱ ተወያይቶ ውሳኔ የሰጠበት መረጃ የተገኘ ሲሆን ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት የተለያዩ ሚዲያ አካላትን በመጋበዝ ፤ ባነሮችን በማሳተም እና በድረገጽ ተደራሽ ያደረጉ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተቋሙ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ሰነዶች ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ማናጅመንት የተወያየባቸው ቃለጉባኤዎች ለክፍሎች የተሰራጩ መሆኑን  ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

በተጨማሪም የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በይፋ ማሰራጨትን በሚመለከት ጋዜጣን እንደሚጠቀሙ መረጃው ያሳያል፡፡ ዘርፉ የሚሰራቸውን ስራዎች ለመገናኛ ብዙኃን፤ ለምርመራ ጋዜጠኝነት እና ሌሎች አካላት መረጃ የሰጡባቸው ሰነዶች መኖራቸውን መረጃዎች ሲያመለክቱ በተጨማሪም ተቋሙ ድረገፅ እና ማህበራዊ ሚዲያ የሚጠቀም መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

## 4.4. አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ

በዘርፉ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አዋጅ እና ደንቦችን በተመለከተ አዲስ የወጡ ወይም የተሻሻሉ መመሪያዎች አለመኖራቸውን መረጃው የሚሳይ ሲሆን ለኃይማኖት እና እምነት ድርጅቶች ማህበራትን በመመዝገብ እና ተዛማጅ አገልግሎትን በመስጠት የወጣው መመሪያ ቁጥር 19/2012 በፍትህ ሚንስቴር መመዝገቡን እና ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ እንዲሁም የዜጎች ቻርተርን በተመለከተ በዘርፉ የዜጐች ቻርተር የተዘጋጀ መሆኑ እና ለተገልጋዩች ተደራሽ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 4.5. የንብረት አስተዳደር

በዘርፉ ካሉት ተቋማት መካከል ሰላም ሚኒስቴር የንብረት አስተዳደር እና መቆጣጠር አሰራር ስርዓት የሆኑት እንደ ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድ፣ ቋሚ ንብረት መመዝገቢያ እንዲሁም አውቶሜሽን በተግባር ላይ የዋሉ መሆኑን እና አመታዊ የንብረት ቆጠራ መካሄዱን መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን የካይዘን ስርአት አለመተግበሩን በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

በ2013 እና 2014 ዓ.ም በዘርፉ የተወገዱ ንብረቶች መኖራቸውን፣ ከመወገዳቸው በፊት በባለሙያ መገምገሙን፣ አስወጋጅ ኮሚቴ መቋቋሙን፣ የተወገዱበት ምክንያት አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ በመሆናቸው መሆኑን እና እንዲወገዱ ውሳኔ የተላለፈባቸው እቃዎችም መጠናቸው ያልታወቀ ቁርጥራጭ ብረቶች ፤226 ጎማዎች፤ 72 ባትሪዎች እና ያገለገሉ 10 መኪናዎች መሆናቸውን፤ አወጋገዳቸውም በጨረታ

እና ለሌሎች ተቋማት በድጋፍ እንዲሰጥ የተወሰነ መሆኑን፤ ድጋፍ የተደረገላቸውም አካላት የድጋፍ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ከሰነድ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ኮምፒውተር እና ተያያዥ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር የሚያስረክቡ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በጨረታ እንዲወገዱ ውሳኔ የተላለፈባቸው ንብረቶች በግልፅ ጨረታ ተጫራቾችን በማወዳደር በአጠቃላይ ብር 693,097.8 (ስድስት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር) መሸጡን የሰነድ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 4.6. የግዥ አስተዳደር

የዘርፉን የግዥ አሰራር ሥርዓት በሚመለከት የግዥ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መዘጋጀቱን እና በየጊዜው ውይይት የሚደረግበት መሆኑን ከቀረቡ መረጃዎች ለማየት ተችሏል፡፡ የ2014 በጀት ዓመት የዘርፉን የግዥ ሂደቱን በሚመለከት 84 በእቅድ የተገዛ፣ 14 ያለዕቅድ የተገዛ፣ 9 በውስን ጨረታ፤ 52 በፐርፎረማ እና 3 በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ ግዢ ያከናወኑ መሆናቸውን መረጃዎች ሲያሳዩ በግዢ ሂደቱ ቅሬታ የቀረበባቸውም ሆኑ የተሰረዙ ግዢዎች አለመኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ የግዥ ሂደትን ለማከናዎን ሰቶክ ላይ ያላውን እቃ በማረጋገጥ እንደሚፈፅሙ ከሰነድ ማስረጃና ከሲስተም ምልከታ ተረጋግጧል፡፡

ከገዥ አሰተዳደር አኳያ በዘርፉ ብዙ ቁጥር የሚይዘው ግዥ የሚፈጸመው በፐሮፎርማ መሆኑ ዘርፉ ለሙስና ተጋላጭነት ያለው እድል ሰፊ ነው፡፡ በመሆኑም ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ሊቀንሱ የሚችሉ የግዥ ዘዴዎችን መጠቀም አለባቸው ፡፡

## 4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር

በዘርፉ ባለው የሰላም ሚኒስቴር የአስተዳደር ኮሚቴዎች ማለትም የቅጥር፣ የዲሲፕልንና የዝውውር የተደራጀ መሆኑን መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን ቅጥርን በተመለከተ ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ይፋ እንደሚያደርጉ ከቀረቡ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

በዚሁ ተቋም በሠራተኛ ድልድል አምስት ቅሬታ ቀርቦ በተቋሙ ቅሬታ ኮሚቴ ምላሽ ቢሰጥበትም ቅሬታ አቅራቢዎቹ ይግባኝ በማለት ወደ ፍርድ ቤት መላኩን ከመረጃዎች ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ሀሰተኛ የትምህርት ማሰረጃዎችንና የሥራ ልምዶችን ከማጣራት እና የሥራ አመራር ምደባ በውድድር ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ እንዲሁም የሙያ ብቃት ማጎልበቻና የሥነ ምግባር ማሻሻያ ስልጠናዎች ለአመራሮችና ሰራተኞች መሰጠቱን የሚገልፅ መረጃ አለመኖሩን ማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የሰው ሀብት መረጃቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለማደራጀታቸው በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከሰው ሀብት አስተዳደር አኳያ የተለዩ ክፍተቶች፡ ሀሰተኛ የትምህርት ማሰረጃዎችንና የሥራ ልምዶችን ከማጣራት እና የሥራ አመራር ምደባ በውድድር ከማድረግ አንፃር ትኩረት ተሰጥቶት የማይሰራ መሆኑ እና

የሰው ሀብት መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደራጀ መሆኑ በዘርፉ እንደስጋት ተወስዷል፤

## 4.8. ሀብት ምዝገባ

የሀብት ምዝገባ መረጃን በተመለከተ በዘርፉ ከአምስት አመራሮች አራቱ፣ ከሁለት መቶ ስልሳ አራት ሰራተኞት ሁለቱ በድጅታል የሀብት ምዝገባ ስርአት ሀብታቸውን ያስመዘገቡ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከሀብት ምዝገባ ስርዓት ጋር በተያያዘ የታዩ ክፍተቶች፡ በዘርፉ ያሉ የተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ሁሉም እንድያስመዘግቡ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩ እንደስጋት ተወስዷል፡፡

## 4.9. ፕሮጀክት አስተዳደር

በዘርፉ ፕሮጀክትን በሚመለከት የቀረበ ሰነድ የለም፡፡

## 4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

በዘርፉ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በየሩብ አመቱ እየተዘጋጀ የሚቀርብ መሆኑን እና በግኝቶች ላይ የተቋሙ ማኔጅመንት ውይይት በማድረግ ተግባራዊነታቸው ላይ ክትትል እና ድጋፍ እንደሚያደርግ እንዲሁም የኦዲት ሪፖርቶች ለሁሉም የሥራ ክፍሎች ተደራሽ እንደሚሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የቀረበው የውስጥ ኦዲት ሪፖርት እንደሚያሳየው ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 60,982,374.25 መሆኑን መረጃዎች ሲያሳዩ የተቋሙን የውጭ ኦዲት ሪፖርት ግን ማግኘት አልተቻለም፡፡

በኦዲት ቁጥጥር አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶች፡ የኦዲት ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊነት ላይ ክፍተቶች መኖራቸው፤

## 4.11. የሙስና ስጋት

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የሰላም ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማት የስራ ክፍሎችና ሂደቶች መደበኛ ስራቸውን ሲያከናዉኑ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን የመለየት፣ የመከሰት ዕድላቸውን እና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችለውን ተጽዕኖ በደረጃ (ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ) በማለት በማስቀመጥ በመጨረሻም የሙስና ስጋት ትንተና ተካሄዷል፡፡

የስራ ክፍሎች የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋት ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መካከለኛና ከባድ በመባል ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ የግምገማ ደረጃው ሙስና በስራ ክፍሎች የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የግዥ እና ፋይናንስ፣ መሰረታዊ አገልግሎት እና የሀይማኖት ምዝገባ የስራ ክፍሎች ከባድ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው ክፍሎች መሆኑን በጥናቱ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የሰው ሃብት ስራ ክፍል አነስተኛ የሆነ ሙስና ስጋት እንዳለበት ከጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## ክፍል አምስት ፡ ምክረ ሀሳቦች

- አዲስ የሆኑ ተቋማት( የብሄራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን ) በስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ ጉልህ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ እና በዚህ ጥናት ላይ በተዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራ፣
- ለስነ ምግባር መከታተያ ክፍል ራሱን የቻለ በጀት የሚመደብበት ሰርዓት መዘርጋት አለበት፣
- ከስራ ክፍሎች የሚቀርቡ የህግ አሰተያየቶች በሚመለከተው የሥራ ክፍል አሰተያየት እየተሰጠበት የሚሄድበት አግባብ ማጠናከር ቢቻል፣
- የዘርፉ ሁሉም ሰራተኞች እና አመራሮች የሀብት መጠናቸውን እና ምንጫቸውን እንድያስመዘግቡ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
- የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋማት ሃላፊዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግበት እና በየጊዜው የሚገመገምበት ሰርዓት ማጠናከር ያስፈልጋል፤
- በፕሮፎርማ የሚገዙ ግዥዎች ቁጥር በመቀነስ የግልፅ ጨረታ አሰራርን ማጠናከር ያስፈልጋል፤
- የካይዘን ስርዓት ተግባራዊ ባልተደረገባቸው ተቋማት ላይ ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ፤
- የሚካሄዱ ግዥዎች በተቻለ መጠን የግልፅ ጨረታ ሰርዓት ተከትለው እንዲሄዱ የዘርፉ እና የተቋማት አመራሮች ትኩረት ሰጥተውበት ቢሰሩ ፤
- ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችና የስራ ልምዶች ከማጣራት አንፃር ፍተሻ በማካሄድ የሰው ሀብት አሰተዳደር ስርዓት ከአድልዎ የፀዳ እንዲሆን የማረጋገጥ ስራ ቢሰራ፤
- በኦዲት አሰራር የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚቀርቡ ምክረ ሀሳቦች ወይም የኦዲት ግኝቶች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ትኩረት ሰጥቶ መስራት።

## ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች

1. የመንግስት መረጃን የህዝብ ተደራሽነት ማረጋገጥ፡- ወቅታዊ እና ትርጉም ያለው መረጃ ማግኘቱን ማረጋገጥ አለባቸው። በሂደት ንድፍ ወቅት በፀረ-ሙስና ተዋናዮች እና በሰላም ሂደት አመቻቾች መካከል የበለጠ ስልታዊ ትብብር ሊፈጠር ይገባል።
2. በፀረ-ሙስና እና ግልፅነት ሰላምና ደህንነትን ማስፈን፡- የሙስና፣ የግጭት እና የአመጽ ለመቀነስ እና በምትኩ ሰላምን ለማስፈን የሚረዳው የጸረ-ሙስና ማሻሻያ ማድረግ ነው። በበጀት ሂደቱ ውስጥ ግልፅነትን

ማሳደግ እና የጥቅም ግጭቶችን ለመለየት እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘዴዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

3. የክትትልና ቁጥጥር ሚዛኖችን ማጠናከር እና የስልጣን ክፍፍልን ማበረታታት፡- የፀረ-ሙስና ተቋማት እና ሌሎች የቁጥጥር አካላት ተግባራቸውን ለመወጣት በቂ ሀብቶች እና ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሰላምን ለመገንባት፣ ሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ እና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የፀረ ሙስና እርምጃ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም የሲቪክ ማህበራት እና ሚዲያዎች ሙስናን ለመመርመር እና የክትትል ተግባርን ለማከናወን አቅም እና ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
4. ሙስናን መዋጋት በጣም ከባድ ስራ ነው ምክንያቱም ምናልባት በጣም ብልህ፣ እውቀት ያላቸው እና ሀይለኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር እየተጋፈጡ መስራትን የሚጠይቅ ስራ በመሆኑ ነው (አንድሪው፣ 2013)፡፡ ስለዚህ የሙስና ተዋጊዎች በስራቸው በጣም ሙያዊ( **Professional Workers**) መሆን አለባቸው፡፡
5. ባለ ሶስት አቅጣጫዊ ስልት መጠቀም፡- መከላከል፣ ትምህርት እና ማስፈጸምን ያጠቃልላል (አንድሪው፣ 2013፣ ICAC፣ 2009) ፡፡ እነዚህን ባለ ሶስት አቅጣጫዊ ስልቶች ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ብዙ ሀገራት ተግባራዊ አድርገዋል(Findlay and Stewart, 1991)፡፡
   i. የመጀመርያው የሙስና መከላከል ሲሆን በመንግስት ሴክተር ያለውን መመሪያ እና አሰራር የመፈተሽ፣ የሙስና ዕድሎችን የመለየት እና ክፍተቶችን ለመድፈን ምክረ ሃሳቦችን የማቅረብ ኃላፊነት ነው፡፡
   ii. ሁለተኛው የማህበረሰብ ግንኙነት ሲሆን ህብረተሰቡን ስለ ሙስና እና እኩይ ተግባራት አስከፊነት በማስተማር ሙስናን ለመዋጋትና ለምርመራው ድጋፍና አጋርነት እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡
   iii. ሦስተኛው፣ ምርመራና ዓቃቤ ሕግ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ተፈጽመዋል የተባሉ ወይም የተጠረጠሩ የሙስና ወንጀሎችን መርምሮ ለፍርድ የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
6. ውጤታማ ከሆኑ የሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች መካከል የስርዓት ቁጥጥርን እና የሰራተኞችን ታማኝነት ማጎልበት፣ የአሰራር ሂደቶችን ማቀላጠፍ፣ ትክክለኛ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ማረጋገጥ እና የሰራተኞች የስነ-ምግባር ደንቦችን ማሳደግ (UNOCD, 2004)፡፡
7. ህብረተሰቡ የሙስና መጥፎነት ለመረዳት እና ለመከላከል የሚያስችል የግንዛቤ ማሰጨበጫ ስልጠና መስጠት፡፡ ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲዎች ድረስ በትምህርት ቤት የሥነ ምግባር ትምህርት ፕሮግራሞች፣ የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ክለብ ማቋቋም፣ የሙስና መከላከል ንግግሮች እና የስነምግባር ማጎልበቻ ሴሚናሮች ለመንግስትና ለግል ሰራተኞች መስጠት፣ በሚዲያ ኮንፈረንሶች እና ቃለመጠይቆችን እንዲሁም ተከታታይ የቲቪ ድራማ መስራት፣ የወጣቶች ትምህርት እና ስነ-ምግባር ማጎልበት ስራ መስራት (አንድሪው, 2013)፡፡

8. በህብረተሰቡ ዘንድ የጸረ ሙስና እርምጃዎችን ለማበረታታት ውጤታማ የሆነ የህዝብ ቅሬታ አፈታት ስርዓት መፍጠር እና የሙስና ሪፖርቶችን በአግባቡ መርምሮ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለበት። ሙስናን ለመዋጋት በአንድ ተቋም ላይ መታመን ውጤታማ ሊያደርግ አይችልም። ይልቁንስ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል እና እያንዳንዱ ተቋም የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት። በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ በሁሉም የመንግስት መምሪያዎች፣ በንግዱ ማህበረሰብ፣ በሙያ ማህበራት፣ በሲቪክ ማህበራት እና በማህበረሰብ አደረጃጀቶች፣ በትምህርት ተቋማት እና በመገናኛ ብዙሃን መካከል ትብብር እና ቅንጅት ሊኖር ይገባል (አንድሪው፣ 2013)።
9. ሙስናን ለመቀነስ ግልጽ የሆነ ከፍተኛ የፖለቲካ ፍላጎት መኖር ኤሲሲዎች እውነተኛ እና ገለልተኛ ተቋማት እንዲሆኑ አስችሏቸዋል (Wing-chi, 2014)። የጸረ ሙስና ተቋማት ምርመራቸውን በሚያደርጉበት ጊዜ ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን አለባቸው። ጠንካራ የፖለቲካ ድጋፍ ወደ ጠንካራ የገንዘብ ድጋፍ መተርጎም አለበት።

# ማጣቀሻ


1. Aidt, T. S. (2003). Economic analysis of corruption: A survey. The Economic Journal, 113, 632–652. http://dx.doi.org/10.1046/j.0013-0133.2003.00171.x.
2. Andrew, H. Y. (2003). Anti-Corruption Strategy of the Hong Kong Special Administrative Region of the People‟s Republic of China. Presentation held at the 4th Regional Anti-Corruption Conference in Kuala Lumpur, Malaysia on 3-5 December 2003
3. Belloni, R., & Strazzari, F. (2014). Corruption in post-conflict Bosnia-Herzegovina and Kosovo: A deal among friends. Third World Quarterly, 35, 855–871. http://dx.doi.org/10.1080/ 01436597.2014.921434.
4. BMZ et al. 2019. Outcome document on results of the ‘Anti-Corruption in Fragile States’ conference. International Conference on Anti-corruption in Fragile States. Berlin, 5 November.
5. Cheng, C. S & Zaum, D. (2013) (eds). Corruption and Post-Conflict Peacebuilding. Routledge.
6. Chibwana C. (2008).Leadership enhancement in agriculture. USA.University of California.
7. Kebede, G. 2013. Political Corruption: Political and Economic State Capture in Ethiopia. European Scientific Journal Vol.9, No.35 ISSN: 1857 – 7881. 23 October 2018.
8. Findlay, M. and Stewart, M. (1991). Implementing Corruption Prevention Strategies through Codes of Conduct. Current Issues in Criminal Justice, 3, (2), 250-264.
9. GIZ. 2020. Anti-corruption in fragile settings: A review of the evidence.
10. Heilbrunn, J. (2004). Anti-corruption commissions: Panacea or real medicine to fight corruption World Bank, Washington DC USA.
11. Hopp-Nishanka, U. 2021b. Corruption and conflict. Breaking the vicious circle from a peacebuilding perspective. FriEnt Working Group on Peace and Development.
12. ICAC (2009). Independent Commission against Corruption. Report on Corruption in the provision and Certification of Security Industry Training.
13. TRANSPARENCY INTERNATIONAL SECRETARIAT IMPLEMENTATION REPORT. Alt-Moabit 96 10559 Berlin Germany ,2013
14. Klitgaard, R. (1988) Controlling Corruption. University of California Press, Berkeley.
15. Global Peace Index (2015). Peace and corruption. New York: Institute for Economics and Peace.
16. Lindberg, J., & Orjuela, C. (2014). Corruption in the aftermath of war: An introduction. Third World Quarterly, 35, 723–736. http://dx.doi.org/ 10.1080/01436597.2014.921421.
17. Mail and guardian Extent of publication Vol. 11, no. 21 (May 19 to 25, 1995)-Subjects Johannesburg (South Africa) – Newspapers
18. Mauro, Paolo (1995).Corruption and Growth Quarterely journal of economics, 110.3.
19. Sáez-Martí, **María** (**2002**). On the cultural transmission of **corruption**. Journal of Economic Theory, 107(2):311-335.

20. Neudorfer, N. S., & Theuerkauf, U. G. (2014). Buying war not peace: The influence of corruption on the risk of ethnic war. Comparative Political Studies, 47, 1856–1886. http://dx.doi.org/10.1177/0010414013516919.
21. Quah, Jon S.T. 2001. Curbing Corruption in Asia: A Comparative Study of Six Countries. Singapore: Eastern Universities Press
22. Shimelis, A. (2005). Corruption and Anti-Corruption in Ethiopia: A case study of the thiopiancustoms authority MA Thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa.
23. Svensson, J. (2005). Eight questions about corruption. The Journal of Economic Perspectives, 19, 19–42.
24. United Nations Convention Against Corruption (UNCAC) ,UNITED NATIONS New York, 2003.
25. The United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC); n the United Nations Office at Vienna, 2004
26. Wing-chi, H. (2004). Combating Corruption: The Hong Kong Experience. Tsinghua china LawReview, 6(239), 239-256
27. Zemelak Ayitenew Ayele, Corruption in Ethiopia: A Merely Technical Problem or a Major Constitutional Crisis? Conference Paper, September 2017 accessed on 02 October 2019.

## አባሪ ሀ፡ የሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

| ተ.ቁ | የሙስና ስጋት የሆኑ ሂደቶች | የመከሰት እድል | ቢከሰት የሚያመጣው ተፅኖ | የሙስና ስጋት | የስጋት መንስኤዎች | የመፍትሄ ሃሳቦች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ግዢ እና ፋይናንስ | ከፍተኛ | ከፍተኛ | ከባድ | የግዢ አዋጁ | በቴክኖሎጂ የታገዘና ግልጽ |
| 2. | መሰረታዊ አገልግሎት | መካከለኛ | ከፍተኛ | ከባድ | ንብረት አስተዳደር | |
| 3. | ሰው ሀብት | ዝቅተኛ | መካከለኛ | አነስተኛ | ምደባ እና | |
| 4. | የሀይማኖት ምዝገባ | መካከለኛ | ከፍተኛ | ከባድ | አመዚጋገብ | |